5ኛ ክፍል ሀብረተሰብ ሳይንስ



የክለሳ ማስታወሻ

አዘጋጅ፣ አብዱ አሊ

መስከረም 2013

አእዋፍ

- በቀለማ ቀለም የተዋቡ ናቸዉ።
- በብዛት የሚገኙት በስምጥ ሸለቆና በዉሀ አካላት ነዉ። ስምጥ ሸለቆዎች ከአዉሮፓና ከኢስያ ፈልሰዉ ለሚመጡ የአእዋፍ መንጋ መልካም የበጋወቅት ማሳለፊያ ናቸዉ።
- በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ እንስሳት
- ብርቅዬ እንስሳት ማለት በአንድ ዉስን መልክዓምድራዊ አካባቢ ብቻ ተገድበዉ የሚኖሩ የእንስሳት ዝርያ ማለት ነዉ።ብርቅዬና ብቸኛ አጥቢዎች በየትኛዉም አካባቢ በአናሳ ቁጥር ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ከፍተኛ ስፍራዎች ይገኛሉ።ለምሳሌ ዋልያ በሰሜንተራሮች ይገኛል። ኒያላ በባሌተራሮች ሳርማ ዛፍ ነ ደኖች ይገኛል። ጭላዳ ዝንጀሮ በሰሜንተራሮች ይገኛል። ምኒልክድከላ በመካከለኛዉ ኢትዮጵያና ገመገም (ከፍተኛስፍራ) እና በባሌከፍተኛ ስፍራዎች ይገኛል። የስዌንቆርኪ በነጭሳር ብሔራዊ ፓርክ በሰንቀሌ መናሐር ይገኛል። የሰሜን ቀበሮ በሰሜን ገመገምና በባሌ ከፍተኛ ስፍራዎች ይገኛል።
- ብርቅዬና ብቸኛ እንስሳት እንደ ዋልያ፣ የሰሜን ቀበሮ፣ ኒያላ የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።በኢትዮጵያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፉ ስለመጣዉ የዱር እንስሳት መጥፋት የሚከተሉት ምክንያቶች በዋናነት ይጠቀሳሉ።
- በእርሻ መሬቶች መስፋፋት
- ከተሞችና እንዱስትሪዎች መስፋፋት
- ህገወጥ አደን
- የግጦሽ መሬቶች መስፋፋት
- ሰደድ እሳት
- ድርቅ

- የዱር እንስሳትና እፅዋት የሚሰጡት ጥቅም
- በዱር እንስሳትና እጽዋት መካከል ተፈጥሮአዊ ሚዛንን መጠበቅ
- በማንኛዉም ስነምህዳር ህይወት ያላቸዉና የሌላቸዉ ነገሮች አብረዉ ይኖራሉ። ህይወት ያላቸዉ ነገሮች በተፈጥሮአዊና በሰዉ ሰራሽ አካባቢዎች የሚኖሩና ተክሎችንና እንስሳት ናቸዉ። ህይወት የሌላቸዉ ደግሞ በተመሳሳይ ስነምህዳር የሚኖሩና ግዑዝ የሆኑነገሮች በሙሉ ያጠቃልላል። ደኖች ለእንስሳት ምግብና መጠለያ በመሆን ያገለግላሉ።
- በሳር ምድሮች ከሚኖሩ ትላልቅ ና ትንንሽ እንስሳት መካከል እንደ አጋዘን ፣ ቀጭኔ፣ የሜዳ አህያ፣ አዉራሪስ፣ አንበሳ፣ ተኩላ፣ አነርና ቀበሮ ትናናሽ እንስሳት ደግሞ እንደ ጥንቸል፣ አይጥ ፤እባብ፣ ና የተለያዩ አእዋፍ መጥቀስ ይቻላል።
- አርሶ አደሮችና የዱር እንስሳት ተስማምተዉ መኖር
- የአርሶ አደሮች ኑሮ ዘለቄታ የሚወሰነዉ የተፈጥሮ አካባቢን በአግባቡ መጠቀም ሲችሉ ነዉ።ዉሀ ፣ አፈር ፣ አለትና የመሳሰሉት ህይወት የሌላቸዉ የተፈትሮ ሀብት ናቸዉ።
- አርሶ አደሮች እንስሳቱ የሚሆሩበትን አካባቢ በተንከባከቡ ቁጥር የአካባቢዉ ተፈጥሮአዊ ሚዛን ይጠበቃል። ይህም በመሆኑ ደግሞ የአፈር ለምነት ይጠበቃል። የከርሰ ምድር ዉሀ መጠን ከፍይላል። የዝናብ መጠን አስተማማኝ ይሆናል። የአፈር ለምነት ይጠበቃል።
- ቱሪዝም ለማህበረሰቡ፣ ለዱር እንስሳትና ለአርሶ አደሮች ያለዉ ጠቀሜታ
- ለኢትዮጵያ ጥበቃ ከሚደረግላቸዉ አካባቢዎች ዉስጥ ብሔራዊ ፓርኮችና መ ናሀሪያዎች ወይም ቤተአራዊት ተብለዉ ይጠራሉ።

- በተፈጥሮ አካባቢዉ የሚገኙ እንስሳት በእኩል ደረጃ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ምክንያቱም ምቾታቸዉን የሚረብሽ ነገር ባለመኖሩና በእንክብካቤና በጥበቃ የተያዙ በመሆኑ ነዉ። የሰሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ከፍተኛዉ የተራራ ጫፍ ራስዳሽን ተራራ ነዉ። ከባህር ጠለል በላይ4620 ሜትር ከፍታ አለዉ።
- ከኢኮኖሚ ጋር ተመጣጣኝ ያልሆነ ፈጣን የህዝብ ቁጥር መጨመር በአፅዋትና በዱር እንስሳት ላይ የሚያመጣዉ አሉታዊ ተፅእኖ
- የእፅዋት መጥፋት
- ለእጽዋት መጥፈት ዋና ዋና ምክንያቶ ችመካከል
- ፈጣን የህዝብ ቁጥር እድገት
- ተጨማሪ የሀብት ፍላጎት
- ኋላቀር የመሬት አጠቃቀም ወዘተ ናቸዉ
- የዱር እንስሳት መሰደድ
- የተፈጥሮ ምቹነታቸዉ የወደመ የዱር እንስሳት አካባቢዉን ለቀዉ ወደሌላ አካባቢ ይሰደዳሉ።
- የተፈጥሮ ምቹነታቸዉ በተፈጥሮአዊ ወይም በሰዎች አማካኝነት ሊወድሙ ይችላሉ።

- **የዱር እንስሳት መሰደድ**
  - ደኖች የሚመነጠሩት ተጨማሪ የእርሻ መሬቶችን ለማግኘትና ለአዳዲስ ሰፈራዎች የቤት ግንባታዎች ለማካሄድ ነዉ ። ደኖች በሰደድ እሳት ሊወድሙ ይችላሉ።
- **የተፈጥሮ እንስሳትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ**
- **የተፈጥሮ እፅዋትና የዱር እንስሳት እንክብካቤ ማለት ተክሎች ከጥፋት በመከላከል በዘላቂነት በአግባቡ መጠቀም ማለት ነዉ።**

- **ድነና**
- ድነና ማለት አንድን አካባቢ ወደ ደንነት መለወጥ ማለት ነዉ። የድነና ስራ የሚከናወነዉ ቀደም ሲል ዛፍ ባልተተከለባቸዉ ስፍራዎች ነዉ።
- መልሶ ድነና
- መልሶ ድነና ማለት ቀደምሲል ተመንጥሮ የነበረን የደን መሬት መልሶ በደን የመሸፈን ሂድት ማለት ነዉ።
- **የደን ቃጠሎን መቆጣጠር**
- በሰደድ እሳት በአንድ አካባቢ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየተዛመተ የሚቀጣጠል እሳት ነዉ። ሰደድ እሳት ከሰዎች እዉቀት ዉጭ በእጽዋትና ደን ላይ የሚነሳ እሳት ነዉ።

- ህገወጥ አደን ያለምንም ፈቃድ የዱር እንስሳትን የመግደል ተግባር ነዉ።
- **የህገ ወጥ አደን መንስኤዎች መካከል**
- በቂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት
- የተፈጥሮ ሀብት
- የግንዛቤ አለመኖር
- ጠባብ የግል ፍላጎት
- ህገ ወጥ አደንን ለመከላከል የሚሆኑ መፍትሔዎችትን በጥንቃቄ መስጠት
- የህዝብ ብዛት እድገትን መቆጣጠር ወዘተ ናቸዉ።